**Concerned Ethiopians in Toronto Coordinating Committee**

998 Bloor St. W, P.O. Box 10666, Toronto M6H 1L8

# ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠናክሮና ትግሉን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲያስተባብር ስምምነት ተደርሶ ውሳኔ በማስተላለፍ ተጠናቀቀ

እሁድ ጁን 10 ቀን 2012 በቶሮንቶ ከተማ 427 Bloor W.est በሚገኘው የ Trinity St. Paul's United Church አዳራሽ፣ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ የጠራው ስብሰባ ተካሂዷል።

አስተባባሪው ኮሚቴውን በመወከል ስብሰባውን የከፈቱት አቶ ቢሹ ማሞ ጥሪውን አክብረው የመጡትን ተሰብሳቢዎች በማመስገን፤ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ አስተባባሪ ኮሚቴ እንዴትና መቼ እንደተመሰረተ ለማስታወስ ያህል ሲያነሱ፤ በኤፕሪል 2001 የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች የወያኔን አገዛዝ በመቃወም ድምጻቸውን ባሰሙበት ጊዜ ወያኔ 41 ተማሪዎችን በግፍ በጨፈጨፈበት ወቅት በቶሮንቶ የሚገኙ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን የተቃውሞ ድምጽ ለማሰማት ያቋቋሙት እንደሆነ በመጥቀስ በወቅቱ በኬንያ በስደት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን በገንዘብ በመርዳት፣ ከዚያ በሁዋላ ላለፉት 11 ዓመታት ሰላማዊ ሰልፎችን በማስተባበር፣ የተቃውሞ ደብዳቤዎች በመጻፍ፣ እንግዶችን በመጋበዝ ህዝባዊ ስብሰባዎችን በማካሄድ፣ የተቃውሞ መግለጫዎችን በማውጣት እስካሁን መቆየቱን በማስታወስ የትግሉ ግለትና ቅዝቃዜ እንዲውም በዲያስፖራ የተከሰቱት ችግሮች በአስተባባሪውም ኮሜቴ እንቅስቃሴ ላይ ሊንጸባረቁ እንደቻሉ ጠቅሰዋል።

ወደ ስብሰባው አጀንዳ ከመገባቱ በፊት በቅድሚያ በሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ/ም ምርጫው ተጭበርብሯል ብለው ሰላማዊ ተቃውሞ ሲያሰሙ በወያኔ ለተጨፈጨፉ ሰማዕታት፤ እንዲሁም በቅርቡ በአርሲ የእስልምና እምነት ተከታዮች ኢትዮጵያውያን ላይ የተደረገውን ግድያ፣ በዋልድባ ገዳም ለእርሻ አይሆንም በሚል ተቃውሞ ሲያሰሙ በወያኔ ታጣቂዎች ሰማእት ለሆኑት ወገኖቻችን፣ በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በቤንቺ ማጂ ዞን፣ በደብረማርቆስ እና በሌሎችም ቦታዎች የወያኔን አገዛዝ በመቃወም የህይወት መስዋእትነት፣ እስራት፣ ድብደባና የግፍ ሰለባ የሆኑትን ኢ/ያን ሁሉ ብድግ ብለው እንዲያስቡ በመጠየቅ ለአንድ ደቂቃ ያህል የህሊና ጸሎት ተደርጎላቸዋል።

በቀጣዩ አቶ ሙሉቀን ሙጬ በወቅቱ የኢትዮጵያ አንኳር አንኳር የሆኑትን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች በፈርጅ በፈርጁ አቅርበዋል። በአገራችን እየታዪና እየተካሄደ ያለው ሁኔታ እጅግ አሳሳቢና አሳዛኝ በመሆኑ አገር ጨርሶ ሳይጠፋ በፊት በውጭ ያለው የአንድነት ሀይል አገር ቤት ያለውን ትግል በመደገፍና በመርዳት ይህን አስከፊ ስርዐት በአንድነት መገርሰስ ይኖርብናል ብለዋል።

ቀጣዩም ተናጋሪ ዶክተር አበበ ወርቁ ሲሆኑ ትኩረት ሰጥተው ያቀረቡት ጥናት በውጭ ያለው ተቃዋሚ የገጠሙት ችግሮች ምን ምን ናቸው? ችግሮቹን ለመፍታት ምን አይነት መንገድ መጠቀም የተሻለና ትክክለኛ ይሆናል? ለችግሮች መፍትሄው ምንድነው በሚለው ላይ የራሳቸውን ጥናትና ምርምር ሰፋ አድርገው ያቀረቡት ትንታኔ የሁሉንም ተሰብሳቢ ስሜት የኮረኮረና በትኩረት የተከታተሉት ሲሆን፣ እሳቸውም ችግሮቹንና መፍትሄዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድና በምሳሌ እያስደገፉ አቅርበዋል። የዶ/ር አበበ ወርቁን ጥናት ተቃዋሚው ክፍል ተለያይቶና

ተበታትኖ ትግሉ የተዳከመበትን ምክንያትና መፍትሄ ስለሚያስረዳ፤ ትምህርታዊ በሆነ መልኩ በተለያዩ ሚዲያዎች ቢወጣ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ከቤቱ ሀሳቦች ተሰጥተዋል።

ውይይቱም በሰፊው ቀጥሎ ብዙ የሀሳብ ልውውጥ ከተካሄደ በሁዋላ ቤቱ፣ የተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ አስተባባሪ ኮሚቴ ጥረት አመስግኖ የሚከተሉትን የውሳኔ ሀሳብ በማጽደቅ ነበር ስብሰባው የተጠናቀቀው።

1ኛ/ ወያኔ ከደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቡን ከርሻው መሬቱና ከቤቱ ነቅሎ በማስገደድ ወደ መጣችሁበት ክልል ሂዱ በማለት የዘር ማጽዳት ወንጀል መፈጸሙን በከፍተኛ ደረጃ በማውገዝ፣ ድርጊቱ ባስቸኳይ እንዲቆም ይጠይቃል። በምዕራብና ደቡብ ኢ/ያ እንዲሁም በአፋር አካባቢ ለልማት ይፈለጋል በማለት ነዋሪውን ህዝብ ያለጥናት፣ ያለተተኪ ቦታና መስፈሪያ ሳይሰጠው የማፈናቀልና መሬቱ ለውጭ አገር ከበርቴዎች መቸብቸቡን ይቃወማል፣ ያወግዛል። በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት ላይ የሚያደርሰውን ግድያና እስራት፣ በጋዜጠኞች፣ በተማሪዎች፣ በሰራተኞች ላይ የሚያደርሰውን ግድያ፣ አፈና፣ እስራት፣ ስቃይና ግፍ ባስቸኳይ እንዲቆም ይጠይቃል።

2ኛ/ በእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ በውስጥ ጉዳያቸውና አመራራቸው ጣልቃ በመግባት በተፈጠረው ተቃውሞ የፈጸመውን ግድያ በማውገዝ፣ የእስልምና እምነት ተከታዮች ያቀረቡትን የመብት ጥያቄ ይደግፋል።

3ኛ/ ጥንታዊና ታሪካዊውን የዋልድባ ገዳም የክርስትና እምነት ስፍራን ለስኳር ፋብሪካ ለማዋል የሚያደርገውን ህገወጥና ታሪክ አፍራሽ ተግባር በማውገዝ፤ የዚህን ገዳም መከበርና መጠበቅ ለመታገል በቁርጠኝነት ከቆሙት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ጋር የቆመ መሆኑን ያረጋግጣል።

4ኛ/ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን፣ ታሪካችንን፣ ቅርሳችንና ባህልናችን ለማጥፋትና ለማውደም የሚጣደፈውን ወያኔን በቆራጥነትና በጽናት ለመታገል፤ አገራችንንም ከገባችበት ችግር ለማውጣት በምናምንበት መንገድና ስልት ሆኖም ግን እጅ ለእጅ ተያይዘን ለመታገልና ለመኳዝ ተስማምተናል።

5ኛ/ በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዐላዊነት የሚያምኑ በተለያዩ ምክንያቶች ከትግሉ ራሳቸውን አግልለው የተቀመጡ፣ በተለያዩ ድርጅቶች የፖለቲካ ሽኩቻ ተሰላችተውና ተስፋ ቆርጠው የሸሹትን፣ በወሬና አሉባልታ ግራ ተጋብተው ቤታቸውን ዘግተው የተቀመጡትን ሆኖም ግን የወያኔን አገዛዝን የሚጠሉና የሚቃወሙትን ሁሉ በደብዳቤና አመቺ በሆነው መንገድ ሁሉ ጥሪ ተደርጎላቸው በአንድ ላይ ተሰባስበን፣ ተመካክረን፣ መጠላለፉን አቁመን የጋራ ጠላታችንን ወያኔን በጋራ እንድንታገል ቤቱ በሙሉ ተስማምቷል።

በመጨረሻም የተቆርቋሪ ኢትዮጵያን በቶሮንቶ አስተባባሪ ኮሚቴ የጀመረው ጥረት እንደሚሳካና በቅርቡ ሰፋ ባለና በተጠናከረ መልኩ ቀጣይ ህዝባዊ ስብሰባ ጠርቶ ጸረ ወያኔ ትግሉን እንደሚያፋፍው እምነት በማሳደር ስብሰባው ተጠናቋል።

ጁን 10 2012
ቶሮንቶ፤ ካናዳ